

በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# ከኦክቶበር 1-10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምግማ

# እንዲሁም ከኦክቶበር 11-20 እና ከኦክቶበር 21-31/2025

# የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦክቶበር 2025

አዲስ አበባ

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣


# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## 1. እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስር ቀናት ለዝናብ መፈጠር ምቹ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከቀን ወደ ቀን እየተስፋፉ ከመምጣታቸዉ ጋር ተያይዞ፤ በተለይም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሁኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ እንዲሁም በክረምት ወቅት ዝናብ ሲያገኙ የነበሩት የሀገሪቱ አከባቢዎች በመጨረሻዎቹ ቀናቶች ላይ የተሻላ ገጽታ ነበራቸዉ፡፡ በመሆኑም፤ በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ዝናብ የሚያገኙት የደቡብ ኦሮሚያ፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች፣ የደቡብ ሶማሌ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ አልፎ አልፎ ጠንከር ያለ የደመና ክምችት ተስተውሎባቸዋል። በተጨማሪም የዝናቡ ሥርጭት ወደ ሰሜን ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ መካከለኛው፣ ሰሜን ምሥራቅና ምሥራቅ ኢትዮጵያ ከመስፋፋቱም ባሻገር አንዳንድ አካባቢዎችም በፀሀይ ኃይል ታግዞ ከተፈጠረው ጠንካራና ዝናብ ሰጪ ደመናዎች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በ24 ሰዓት ውስጥ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል። በተጨማሪም በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ20 ሚ.ሜ በላይ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል አርባ ምንጭ 23.4፣ ባህር ዳር 35.2፣ 46.2፣ 33.8፣ ጎሬ 29.2፣ ነገሌ 13.6፣ 22.3፣ ነቀምት 25.4፣ አዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ 23.4፣ አዲግራት 20.8፣ አይራ 22.2፣ አልጌ 25፣ 23.5፣ 35፣ አንገር ጉትን 20፣ አርጆ 24.6፣ 28.8፣ አሶሳ 34.7፣ በደሌ 20.2፣ ቦሬ 36፣ ቡለን 27፣ 20.2፣ 38.4፣ 20፣ 20.8፣ ቡራ 28.1፣ 28.8፣ 60.5፣ ቡርጂ 27.6፣ ቻግኒ 25.4፣ 30.5፣ ጨዋቃ 22፣ 28፣ ዳንግላ 20.4፣ ደምቢ ዶሎ 23.8፣ ዶሎመና 20.7፣ 20.4፣ 20.3፣ ኢጃጂ 47.7፣ ጋቲራ 20.2፣ ጊዳ አያና 21.6፣ ጊምቢ 25.5፣ ጎሎልቻ 20፣ ቡሌ ሆራ 26፣ 21፣ 25.2፣ ጃራ 20፣ ላሬ 31.4፣ ሊሙገነት 57.5፣ ነጆ 34.4፣ ሻምቡ 35.8፣ ሽሬ 29.5፣ 38.4፣ ሲሪንቃ 26.2፣ ቴፒ 54.8፣ አቦ ሞሪንጋ 29.2፣ 22.2፣ አጋሮ 22.5፣ 22፣ አንጋጫ 24.5፣ 23.5፣ አታንጎ 25፣ 28.7፣ 49፣ በቆጂ 22.3፣ ቢላምቢሎ 23.4፣ 23.3፣ 22.7፣ 33፣ ቦርቃ 24.6፣ ቡሬ 22፣ ጉበይሬ 75.6፣ ጉበቲ 22.7፣ 34.7፣ 33.9, ሃሮ 30.2፣ ቅዳሜ ገበያ 26.8፣ 27.6፣ 48.8፣ 22.4፣ 37.6፣ 58.6፣ 59.8፣ ኮበን 33፣ ኩሚ 21.1፣ መካነ ኢየሱስ 23.8፣ ኦንጋ 43.3፣ 26.5፣ 42.6፣ 28.3፣ ሸቤ 20.5፣ ተርቆዲ 23.7፣ 36.8፣ ትንሹ ሜጢ 31.3፣ መንደር አስራ ሶስት 20.2፣ 20.4፣ መንደር አስራ አንድ 46፣ 53.5፣ ያንፋ 40.3፣ 30.3፣ 37.8፣ 30.3፣ 28.2፣ 37.8፣ ያዮ 21.7፣ 24.6፣ 42.5፣ እንዲሁም ይርጋለም 28.6 ሚ.ሜ የሚደርስ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።

## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣
## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በሃያ ሰባት (27) የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡ በተጨማሪም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታች በሁኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ አከባቢዎች እንዲሁም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 40.3 - 75.6 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል ጉበይሬ፣ ቡሬ፣ ቅዳሜ ገበያ፣ ሊሙ ገነት፣ ተፒ፣ መንደር አስራ አንድ፣ አታንጎ፣ ኢጃጂ፣ ባህር ዳር፤ አንጋ፣ ያዮ እና ያንፉ ይገኙበታል (ምስል 1)፡፡





ምስል፡1 ከአፐክቶበር 1-10 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ35 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ


# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

ባለፉት አስር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት አከባቢዎች የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል የቦረና፣ የምስራቅ ቦረና፣ የጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፣ ከሱማሌ ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር ዞኖች ላይ ከ21-100 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ3-6 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡ በተመሳሳይ ቀደም ብሎ የክረምት ወቅት ዝናብ እያገኙ የነበሩት ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ባሌ፣ ምዕራብ ሐረርጌ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ምዕራብና ደቡብ ጎንደር፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የአዊ፣ የባህርዳር ዙሪያ ዞኖች፣ የዋግ ህምራ፣ የደቡብ እና የሰሜን ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዠንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች ላይ ከ41-281 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ3-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡ በተጨማሪም ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ደቡብ ምስራቅና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጎፋ፣ የወላይታ እና ጌዲዮ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል የጋቢ፣ ፋንቲ፣ አዉሲና ማሂ ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል የሲቲ እና የኤረር ዞኖች ላይ ከ11-40 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-4 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡





ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2025 ድረስ ዝናብ የዘነባባቸዉ ቀናት


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ ከሆኑት አከባቢዎች ከኦሮሚያ ክልል የቦረና፣ የምስራቅ ቦረና፣ የጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፣ ከሱማሌ ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር ዞኖች ላይ በአብዛኛዉ መደበኛና ከመደበኛው በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3)፡፡ በተመሳሳይ ቀደም ብሎ የክረምት ወቅት ዝናብ እያገኙ የነበሩት ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ባሌ፣ ምዕራብ ሀረርጌ ዞኖች፣ ከአማራ ክልል ምዕራብና ደቡብ ጎንደር፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የአዊ፣ የባህርዳር ዙሪያ ዞኖች፣ የዋግ ህምራ፣ የደቡብ እና የሰሜን ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ደቡብ ምስራቅና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጎፋ፣ የወላይታ እና ጌዲዮ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል የጋቢ፣ ፋንቲ፣ አዉሲና ማሂ ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል የሲቲ እና የኤረር ዞኖች ላይ በአብዛኛዉ መደበኛና ከመደበኛው በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

## 1.2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባለፉት አስር ቀናት በተለይም በመጨረሻዎቹ ቀናቶች በደቡብ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በመካከለኛው፣ በሰሜን ምሥራቅና በምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተገኘው በመጠንም ሆነ በስርጭት የተስፋፋ ዝናብ የአፈር ውስጥ እርጥበትን አሻሽሏል፡ ፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም ቀደም ሲል ተዘርተው ፍሬ በመሙላት እና በማበብ ላይ ለሚኙት እንደ ማሽላና በቆሎ ላሉት የረጅም ጊዜ ሰብሎችም ሆነ ለሌሎች የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለፍራፍሬዎችና ለጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተለይም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተገኘው እርጥበት ጥምር ግብርና ለሚያከናውኑ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ለማከናወንም ሆነ ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታ የፈጠረ ነበረ። እንዲሁም በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ ቆላማው አካባቢ ለሚኖሩ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች በቂ የግጦሽ ሣርና የመጠጥ ውኃ አቅርቦት እንዲኖር ከማስቻል አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው (ካርታ 4) ፡፡




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 1.3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት በአብዛኛው ኦሞ ጊቤ፣ ባሮ አኮቦ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ መካከለኛው እና ታችኛው ተከዜ፣ አባይ፣ አይሻ፣ መረብ ጋሽ፣ በጥቂት የላይኛው አዋሽ፣ በላይኛውና መካከለኛው ዋቤ ሸበሌ እንዲሁም ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገጸ ምድር የውሀ ፍሰት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በመካከለኛው ተከዜ፣ በጥቂት የላይኛው አዋሽ፣ በታችኛው ዋቤ ሸበሌና ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ የሆነ የገጸ ምድር የውሃ ፍሰት ነበር፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት ቀናት የነበረው እርጥበት የገጸ ምድርም ሆነ የከርሰ ምድር የውሃ ሀብት እንዲሻሻል በማድረግ ወደ ግድቦችና የተለያዩ የውሃ ማጠራቀሚያዎች የገባው የዉሃ መጠን እንዲጨምር ከማደረግ አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ ይህም ሁኔታ ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ ለሃይል ማመንጫነት እንዲሁም ለመስኖ ግድቦች የተሻለ የውሃ ግብዓት እንዲኖር ያስቻለ እንደነበረ የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ (ካርታ 5) ።





ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 2. መግቢያ


የበጋ ወቅት ከኦክቶበር እስከ ጃንዋሪ ያሉትን ወራት የሚያካትት ሲሆን፤ ለደቡብና ደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ነው፡፡ የበጋ ወቅት ከዓመታዊ የዝናብ መጠኑ እስከ 45% የሚደረሰውን የሚሸፍን ሲሆን ከበልግ ቀጥሎ የተሻለ ዝናብ የሚኖርበት ወቅት ነው። በወቅቱ ከሚኖረው የዝናብ መጠን ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዘው በኦክቶበር እና በመጀመሪያዎቹ በኖቬምበር አስር ቀናት የሚጥለው ዝናብ ነው። በዚህ ወቅት ከፍተኛ መጠን ያለው የዝናብ መጠን የሚኖረው በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ አካባቢዎች ላይ ነው። በመደበኛ ሁኔታ በሀገሪቱ ደቡባዊ አጋማሽ ላይ የበጋ ወቅት ዝናብ ከኦክቶበር መጀመሪያዎቹ ቀናቶች ጀምሮ መዝነብ ይጀምራል፡፡ በመደበኛ ሁኔታ በኦክቶበር የሁለተኛዉ አሥር ቀናት የክረምት ድንበር (ITCZ) ወደ ደቡብ አቅጣጫ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በደቡብ የሀገሪቱ አጋማሽ ላይ እየተጠናከሩ ይሄዳሉ፡፡ ስለሆነም የደቡብ እና የደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ በተጠናከረ ሁኔታ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውን ያገኛሉ፡፡

## 2.1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በሚቀጥሉት የኦክቶበር ሁለተኛዉ አሥር ቀናት አሁን ከሚታዩትና በቀጣይነትም የተተነበዩት የትንበያ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ዝናብ ሰጭ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በደቡብ፣ ምስራቅ፣ ደቡብ ምዕራብና ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የምስራቅ ቦረና፣ የምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡ በተጨማሪም ቀደም ብሎ የክረምት ወቅት ዝናብ እያገኙ የነበሩት የምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ እንዲሁም የሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በፀሀይ ሀይል ታግዘው ከሚጠናከሩት የደመና ክምችቶች ላይ በመነሳት በምዕራብ፣ በመካከለኛዉ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በ24 ሰዓት ውስጥ ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ የሚደተርስ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ይኖረቸዋል (ካርታ 6 እና 4)፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 11-20, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 11-20, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች | | |
|---|---|---|
| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናብ መጠን |
| አሮሚያ | ምስራቅ ቦረና፣ ጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ጃራር፣ ነጎብ፣ ዶሎ፣ ቆራሂ፣ ሸበሌ፣ አፍዴር፣ ሊበን እና ዳዋ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| የክረምት ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ ዞኖች | | |

| | | |
|---|---|---|
| ኦሮሚያ | የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ ዞኖች | መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| | ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ የሰሜን እና የምዕራብ የሸዋ ዞኖች፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ) |
| አማራ | የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም፣ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ) |
| | የዋግ ህምራ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የሰሜን እና ደቡብ ወሎ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ትግራይ | የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛዉ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | የአኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| አፋር | የማሂ፣ ሀሪ፣ ቅልበቲ፣ ፈንቲ እና ጋቢ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | የወላይታ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ሲቲ፣ ፋፈን እና ኤረር ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |

## 2.2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመጪዎቹ የኦክቶበር ሶስተኛዉ አሥራ አንድ ቀናት አሁን ከሚታዩትና በቀጣይነትም የተተነበዩት የትንበያ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ዝናብ ሰጭ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ፣ ምስራቅ፣ ደቡብ ምዕራብና ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረና እና ምስራቅ ቦረና ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ላይ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም ቀደም ብሎ የክረምት ወቅትን ዝናብ እያገኙ በነበሩት በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ እንዲሁም በምስራቅ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

## 2.3 እ.አ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ እንዲሁም በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚኖረው የክረምቱ ቀጣይነት ያለዉ እርጥበት ለወቅቱ የግብርና ስራ እንቅሥቃሴ በአመዛኙ አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል። እንዲሁም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ምስራቅ ቦረና፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ላይ የሚጠበቀው ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት በአካባቢው ለሚጀምረው የግብርና እንቅስቃሴ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በተጨማሪም ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስና የሚኖሩትን መልካም አጋጣሚዎች በላቀ ሁኔታ ለመጠቀም የቀረቡትን ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በሁሉም ደረጃ በተገቢው ሁኔታ መተግበር ያስፈልጋል።

ሠንጠረ ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| ዞኖች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| **የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ የመኸር አምራች ዞኖች** | | | | |
| የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም፣ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛዉ፣ ትግራይ ዞኖች፣ የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ፣የአኝዋክ፣ መዠንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ ፣የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • እንደ ሽንብራና ጓያ የመሳሰሉ የጥራጥሬ ሰብሎችን ለመዝራት<br>• ዘግይተው ተዘርተው ፍሬ በመሙላት ላይ ላሉ ለረጅምና መካከለኛ ጊዜ ሰብሎች እድገት<br>• ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳር ዕድገት<br>• የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሟላት | • እንደ ዋግ የመሳሰሉ የሰብል በሽታ መከሰት<br>• የአረም መከሰት | • የደረሱ ሰብሎችን በጊዜ መሰብሰብ<br>• የጥራጥሬ ሰብሎችን በጊዜ መዝራት<br>• የማሳ ጉብኝት በተከታታይ ማከናወን<br>• ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ ጋር በመመካከር የአየር ሁኔታ ምቹነትን ባገናዘበ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ<br>• አረምን በወቅቱ መከታተል እና ማረም |
| **በልግ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውና የመኸር አብቃይ የሆኑ ዞኖች** | | | | |
| ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ የሰሜን እና የምዕራብ የሸዋ ዞኖች፣ ባሌ ፣ ምስራቅ ባሌ፣ የዋግ ህምራ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የሰሜን እና ደቡብ ወሎ ዞኖች ፣ወላይታ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ፣ የፋፈን ሲቲ እና ኤረር ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • እንደ ሽንብራና ጓያ የመሳሰሉ የጥራጥሬ ሰብሎችን ለመዝራት<br>• ዘግይተው ተዘርተው ፍሬ በመሙላት ላይ ላሉ ሰብሎች እድገት<br>• ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳር ዕድገት<br>• የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • የደረሱ ሰብሎችን ለመሰብሰብ አስቸጋሪ ሁኔታ መኖር<br>• እንደ ዋግ የመሳሰሉ የሰብል በሽታ መከሰት<br>የአረም መከሰት | • የደረሱ ሰብሎችን በጊዜ መሰብሰብ<br>• የጥራጥሬ ሰብሎችን በጊዜ መዝራት<br>• ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ ጋር በመመካከር የአየር ሁኔታ ምቹነትን ባገናዘበ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ<br>• አረምን በወቅቱ መከታተል እና ማረም |
| ጉራጌ፣፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ የማሂ፣ ሀሪ፣ ቅልበቲ፣ ፈንቲ እና ጋቢ ዞኖች የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ | ቀላል መጠን ያለዉ እርጥበት | • የእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት በመጠኑ መሻሻል | • የአፈር ዉስጥ እርጥበት መጠነኛ መሆን | • የደረሱ ሰብሎችን በጊዜ መሰብሰብ<br>• የጥራጥሬ ሰብሎችን (ሽንብራ እና ጓያ) መዝራት |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| በጋ ሁለተኛ የዝናብ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች | | | | |
| ጃራር፣ ነጎብ፣ ዶሎ፣ ቆራሂ፣ ሸበሌ፣ አፍዴር፣ ሊበን፣ ዳዋ ፣ጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ ፣ደቡብ ኦሞ ፣ምስራቅ ቦረና፣ ጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ እና ሁሉም ሲዳማ የክልሉ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • የዝናብ ውሃ ለማሰባሰብና ለማጠራቀም<br>• ለደጋማ አካባቢዎች ዘር ለመዝራት<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • የአፈር ዉስጥ እርጥበት መጠነኛ መሆን | • የዝናብ ውሃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል<br>• ደጋማ አካባቢዎች ላይ ዘር መዝራት |

## 2.4 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በቀጣይ የኦክቶበር ሁለተኛ አሥር ቀናት በኦሞ ጊቤ፣ በአባይ፣ በባሮ አኮቦ፣ በኦጋዴን፣ በስምጥ ሸለቆ፣ በላይኛው እና መካከለኛው አዋሽ፣ በገናሌ ዳዋ፣ በዋቤ ሸበሌ እነዲሁም በመካከለኛው እና ታችኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ መካከለኛ መጠን ያለው የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ይጠበቃል። በመሆኑም የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት ሊኖር የሚችለው መልካም ዕድሎችን ለመጠቀም የሚከተሉትን ተፋሰስ ተኮር የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በሚቀጥለው ሰንጠረዥ ይመለከቱ፡፡

ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሃዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| የውሀ ተፋሰሶች | የገጸ ምድር የውሃ ሽፋን | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውሀ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| በአብዛኛው ኦሞ ጊቤ፣ አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ ኦጋዴን፣ ስምጥ ሸለቆ፣ በላይኛው እና መካከለኛው አዋሽ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ዋቤ ሸበ | መካከለኛ እርጥበት | • የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን መሻሻል<br>• የመስኖም ሆነ የሃይል ማመንጫ ግድቦች ውሃ መጠን መጨመር | የፍሳሽ መውረጃዎች በጠጣር ቆሻሻ መዘጋት | • ፍሳሽ ሊዘጉ የሚችሉ ቆሻሻዎች በተገቢ ሁኔታ ማስወገድ<br><br>የዝናብ ውሀ ማሰባሰብና ማጠራቀም |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| እና በመካከለኛው እና ታችኛው ተከዜ | | የገፀ ምድርም ሆነ የከርሰ ምድር የውሃ ሀብተ መጨመር | | |
| በአብዛኛው አፋር ደናክል፣ አይሻ፣ መረብ ጋሽ፣ በመካከለኛው እና ታችኛው ገናሌ ዳዋ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ በታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆና ላይኛው አባይ | ከመጠነኛ እስከ ደረቅ ሁኔታ | • የጎርፍም ሆነ የደለል ስጋት አለ መኖር<br>• የሚገኘው መጠነኛ እርጥበት የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • ዝቅተኛ የውኃ ፍሰት<br>• በቆላማ አካባቢዎች በትነት ምክንያት የውሃ መጠን መቀነስ | • የሚገኘው መጠነኛ የዝናብ ውሃ ከጣራ እና ከመሬት ወለል በተግቢ ሁኔታ ማሰባሰብ<br>• የውሀ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም<br>• የሚገኘውን መጠነኛ የዝናብ ውሀ ከብክነት እና ከብክለት መከላከል |